# የአለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት አካሔድን አስመልክቶ የሚነሱ የትኩረት ነጥቦች

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የፍትሐ ብሔር ዳይሬክቶሬት

አዘጋጅ፦ ዮናስ መስፍን

የካቲት **2010**

## መነሻ ጥያቄዎች

1. የግልግል ዳኝነት ስምምነት ዉል ተፈራርመህ/ሽ ታዉቂያለሽ/ህ?
2. አንድን የግልግል ዳኝነት ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ነዉ የሚባለዉ ምን ሲሆን ነዉ?
3. የግልግል ዳኝነት ስምምነት ወሰን ምን አይነት ነገሮች ላይ ያተኩራል?
4. የግልግል ዳኝነቱ የሚመራበት ህግ ምንን ይወስናል?
5. በግልግል ዳኝነት ዉስጥ የተዋዋይ ወገኖች የመዋዋል ነፃነት በምን ይወሰናል?
6. የግልግል ዳኝነቱን ህጋዊ መቀመጫ የሚመርጥ ማን ነዉ?
7. የግልግል ዳኝነቱን ዳኞች ወይም ተቋማት ስንመርጥ ከግንዘቤ ማስገባት ያለብን ነገሮች ምን ምን ናቸዉ?
8. በግልግል ዳኝነት ሂደት ዉስጥ የሚተገበረዉ የስነ ስርዓት ህግ የማን ሀገር ነዉ? የሚወስነዉ ማን ነዉ?
9. የእግድ እና ሌሎች ግዚያዊ ትዕዛዞችን በግልግል ዳኝነት ሂደቱ የመስጠት ስልጣን የማን ነዉ?
10. የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ ሆኖ የተመረጠዉ ሀገር በግልግል ዳኝነት ሂደቱ እና በግልግል ዳኝነቱ ዉሳኔ አፈፃፀም ላይ ሊኖረዉ የሚችለዉ ተፅዕኖ ምን ሊሆን ይችላል?
11. በግልግል ዳኝነቱ ሊፈታ የታሰበዉን ግጭት ለመወሰን ዳኞች የሚተገብሩት መሰረታዊ ህግ እንዴት ይመረጣል? የጉባኤዉ መቀመጫ ሀገር አስገዳጅ ህጎች የትኞቹ ናቸዉ?
12. የግልግል ዳኝነቱን ዉሳኔ ለማሻር የሚያበቁ ምክንያቶች የትኞቹ ናቸዉ?
13. የግልግል ዳኝነቱ ዉሳኔ እንዳይፈፀም ለመቃወም የሚያበቁ ምክንያቶች የትኞቹ ናቸዉ?

መግቢያ

ኢትዮጵያ በምትገባቸዉ አለም አቀፍ የግንባታ፣ የግዥ፣ የኢንቨስትመንት እና ሌሎች ዉሎች የግልግል ዳኝነት ከዉሉ በሚነሱ አለመግባባቶች ላይ እንደ ግጭት መፍቻ መንገድ እንዲያገለግል ታስቦ በዉል ተካቶና አካል ሆኖ እናገኘዋለን። ነገር ግን በአለም አቀፍ ዉሎች ላይ አለመግባባት ሲፈጠር ኢትዮጵያ በፈረመቻቸዉ አለም አቀፍ የግልግል ስምምነቶች መሰረት የሚገባትን ዳኝነት ሳታገኝ ዉጤታማ ሳትሆን ቀርታለች። ዉጤታማ ያለመሆኑ ምክንያት በዋናነት አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነትን ጥልቀት ባለዉ መንገድ አለማወቅ እና የግልግል ስምምነቱ ሲፈረም እንደ ተዋዋይ ወገን ጥቅምን በሚያስጠብቅ መልኩ ስለማይፈረም ነዉ። በዚህ ወቅት አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ስምምነትን በአለም አቀፍ ደረጃ በሚገቡ ዉሎች እንደ ግጭት መፍቻ ስርዓት ማስገባት አማራጭ የሌለዉ ነገር ነዉ። የሚሻለዉ ነገር ስለ ጉዳዩ በቂ እዉቀት ማዳበር እና በተግባራዊነቱ ላይ ሊገጥሙ ስለሚችሉ ፈተናዎች ግንዘቤ መያዝ ነዉ። ይህንን ችግር በተወሰነ መልኩም ቢሆን ለመፍታት የሚያስችለዉ ስለ ጉዳዩ ግንዛቤን ሊጨምሩ የሚያስችሉ ስልጠናዎችን ማዘጋጀት ነዉ። ለዚህም ሲባል በአለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ከሚነሱ ንድፈ ሃሳብ ተኮር ተለምዶአዊ የስልጠና ፅሁፎች ለየት ባለ መልኩ ይህንን ጽሁፍ ለማዘጋጀት ጥረት ተደርጓል። የዚህ ጽሁፍ ትኩረት አለምአቀፍ የግልግል ዳኝነትን ተግባራዊ አካሔድ በመፈተሽ ከስምምነቱ አትራፊ መሆን የሚቻልበተን መንገድ ለመጠቆም ነዉ።

አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ማለት ምን ማለት ነዉ? አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት በሁለት ወገኖች መካከል አንድ አለማቀፋዊ ይዘት ያለዉን ጉዳይ በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ የሚደረግ የግጭት አፈታት ዘዴ ነዉ። አለም አቀፍ ይዘት ያለዉ ሲባል ተከራካሪ ወገኖች ከተለያዩ ሀገሮች ወይም ህግ ግዛት የመጡ ሲሆኑ እና አከራካሪዉ ጉዳይ ከአንድ በላይ ከሆነ ሀገር ጋር የተነካካ ማለት ነዉ። የግልግል ዳኝነት ቦታዉ፣ ዋናዉ ዉል የሚፈፀምበት፣ ለግልግል ምክንያት የሆነዉ ግጭት ከተዋዋይ ወገኖች መደበኛ የንግድ ቦታ ካለበት ሀገር ዉጭ መሆኑ ወይም በአንዳንድ ሀገር ህጎችም ተዋዋይ ወገኖች ግልግሉ ዓለም አቀፍ እንዲሆን ከተስማሙ የግልግል ዳኝነቱ ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ይሆናል ማለት ነዉ። አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት በብዙ ሀገሮች በተለየ የህግ ማዕቀፍ የሚተዳደር ዘመናዊነትን የተላበሰ ሲሆን በኢትዮጵያ ግን አሁን ያለዉ ህግ በሚገባ የሚገዛዉ እና እዉቅና የሰጠዉ አይደለም። የዚህ አይነቱ የግልግል ዳኝነት የጎላ ጠቀሜታ ያለዉ አለም አቀፍ የንግድ ግጭቶችን እና የኢንቨስትመንት አለመግባባቶችን በመፍታት ነዉ። በዚህ አይነት ጉዳዮች የግጭት መፍቻ ስርዓት በፍርድ ቤት ከሚካሄዱ ክርክሮች/ሙግቶች በተለየ የሚሰጠዉ ጠቀሜታ የሚከተሉት ናቸዉ። ከዋነኞቹ ጥቅሞች ዉስጥ ሚስጥር ጠባቂነቱ፣ ገለልተኛ ዳኛ ለማግኘት ማስቻሉ እና ለአፈጻጸም ቀላል መሆኑ በአለም አቀፍ ንግድ እንቅስቃሴ ዉስጥ የጎላ ሚና እንዲኖረዉ አድር Õ ል። ከዚህም የተነሳ አለም አቀፍ የንግድ እንቅስቀሴ በአለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ላይ መመርኮዝ ከጀመረ ቆይቷል።

ከዚህ ክፍፍል በተጨማሪም የግልግል ዳኝነቱን በሚመለከተዉ ጉባኤ/ችሎት ተቋማዊ ሁኔታ በመነሳት የግልግል ዳኝነት ጊዜያዊ (Ad hoc arbitration) እና ተቋማዊ(institutional) በመባል በሁለት ይከፈላል። አለማቀፋዊ የግልግል ዳኝነት በአለም የንግድ እንቅስቃሴ ላይ ያለዉ ተጽዕኖ እያደገ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ተቋማዊ ግልግል በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍቶ ይገኛል። በጣም ታዋቂ ከሆኑ አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ተቋማት ዉስጥ ዓለም አቀፍ የንግድ ቻምበር(International chamber of commerce ICC)፣ ፣የዓለም ንግድ ድርጅት(World trade organization) ፣ የዓለም የአዕምሮ ፈጠራ ባለንብረትንት ድርጅት(WIPO)፣ ለንደን የአለም አቀፍ ግልግል ፍርድ ቤት(LCIA)፣ እና ሌሎችም ሲሆኑ በኢትዮጵያ ደግሞ አዲስ አበባ ንግድ ቻምበር የግልግል ተቋም የሚጠቀሱ ናቸዉ። የግልግል ዳኝነት ተቋማት በሚሰጡት የፍርድ ብስለት፣ጥራት እና ባላቸዉ አባላት ብዛት ምክንያት የአገልግሎት አድማሳቸዉ በጣም የሰፋ እና ዉሳኔያቸዉም በፍርድ ቤቶች በቀላሉ የሚፈጸም ነዉ። አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ስምምነቶች በተለያየ መልኩ ሊገቡ ይችላሉ። በሀገራት መካከል በሚገቡ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመን ስምምነቶች ለምሳሌ፡- ኢትዩጵያ የገባቻቸዉ የሁለትዮሽ ስምምነቶች እና የኢንቨስትመንት ስምምነቶች፤ በዉል ስምምነት የሚገቡ ሰዎች እንደግጭት መፍቻ ስርዓት በዉላቸዉ ሲያስቀምጡት ወይም ግጭት ከተከሰተ በኋላ ተከራካሪ ወገኖች በሚገቡት ዉል መሰረት ሊገባ ይችላል። በዚህ ፅሁፍ ግን ትኩረት የምናደርገዉ አለም አቀፍ የንግድ ግልግል ዳኝነትን ሆኖ የኢንቨስትመንት ጉዳዮችን አንመለከትም ። በ UNCITRAL ሞዴል ህግ አንቀጽ 1 ትርጉም መሰረት የንግድ ጉዳዮች፡- የንግድ ባህሪ ያላቸዉን ከዉል ወይም ከዉል ዉጭ በሚፈጠሩ ግንኙነቶች ማለትም እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ለማቅረብ፣ ለማከፋፈል፣ ለመከራየት፣ በኮሚሽን ለመሸጥ፣ የግንባታ ስራዎችን ለመስራት፣ የማማከር ስራዎችን፣ ከፋይናንስ አገልግሎት፣ ከማምረት ስራ ጋር ተገናኙ፣ የትራንስፖርት ስራዎችን ከመስራት እና ከኢንቨስትመንት ጋር የሚገናኙ ግንኙነቶችን ሁሉ ሊያካትት ይችላል። ስምምነት ሲገባ ከመጀመሪያዉ ግልግል ዳኝነት መሆኑ ከሌሎች አማራጮች ያለዉ ጠቀሜታ እና ተፈፃሚነቱን ቀድመን ማሰብ የግድ የሚል ነዉ። ህግ መረጣ እና መቀመጫ መረጣ ላይ የእግድ እና ግዚያዊ ትዕዛዞች መኖር አለመኖራቸዉ፤ መቻል አለመቻላቸዉ ከግንዛቤ ዉስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ ነዉ።

በዋናዉ ዉል ስለ ግጭት አፈታት መንገድ/አማራጮች ምንም የተባለ ነገር ከሌለ ደግሞ ግጭቱን ለመፍታት የሚመረጠዉን አማራጭ ለየት ባለ ሁኔታ ማየት አስፈላጊ ነዉ። ለምሳሌ፡- ወደ ግልግል ስምምነት መግባቱ ባለ እዳነትን ብቻ የሚያተርፍ ከሆነ ወይም ወደ ግልግል ዳኝነቱ

መግባት ከትርፉ ኪሳራዉ የሚበዛ ከሆነ ቀድመን ሌሎች አማራጮችን ለማማተር የተሻለ እድል ስለሚሰጥ በዋናዉ ዉል ከሚገባዉ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ከሚፈጠረዉ ጫና እና የመደራደር አቅም ማነስ ስለሚወጣ ላቅ ባለ የድርድር አቅም መደራደር ያስፈልጋል። አንዳንዴ በዚህ አይነት ሁኔታ ከግልግል ዳኝነቱ ይልቅ በሀገሪቱ(ኢትዮጵያ) መደበኛ ፍርድ ቤትእንዲታይ መተዉም ሀገራዊ ጥቅምን ከማስጠበቅ አንፃር ከፍተኛ ሚና ሊኖረዉ ይችላል።

የሆነዉ ሆኖ የግልግል ዳኝነት ከሌሎች የግጭት አፈታት ስርዓቶች በተሻለ ጥቅም ይሰጣል ከተባለ ወደ ስምምነቱ ሲገባ ትኩረት ሊሰጣቸዉ የሚገቡ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸዉ። በሀገራት መካከል ከተገቡት ከተከራካሪ ወገኖች ቁጥጥር ዉጭ ያሉ ዉሎች እንደተጠበቁ ሆኖ ወደ አለም አቀፍ ዉሎች የሚገቡ ወገኖች የግልግል ስምምት አንቀጽ በዉላቸዉ ሲያስገቡ ትኩረት የሚያደርጉባቸዉ ነጥቦች የሚከተሉት መሆን አለባቸዉ።

1. የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ወሰን/

የግልግል ዳኝነት ለግልግል ዳኝነት ብቁ የሆኑ ጉዳዮችን /arbitrable matters/ ለመፍታት የሚረዳ ቢሆንም አለምአቀፍ የግልግል ዳኝነት ደግሞ ከአለም አቀፍ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ግጭቶችን ለመፍታት ይረዳል። አለምአቀፍ ኢንቨስትመንት ግንኙነቶች ኢንቨስት በሚደረግበት ሀገር መንግስት እና በዉጭ ኢንቨስተሩ መካከል በሚደረግ ዉል ወይም ኢንቨስተሩ ከሚመጣበት ሀገር እና ኢንቨስተሩን በሚያስተናግደዉ ሀገር መካከል በሚፈረም የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶችን መሰረት ሊያደርግ ይችላል። በእርግጥ ይህንን ግንኙነት ተቀባይነት ያላቸዉ የዉጭ ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ መርሆች እና ህጎች ወይም በብዙ ሀገራት በአንድነት የተፈረሙ ስምምነቶችም ገዥነት አላቸዉ። የንግድ እና ኢንቨስትመንት ግንኙነቶች በዋናነት ከዉል የሚመነጩ ናቸዉ። በዚህ ግንኙነት ግን ከዉል ዉጭ የሚመጡ ሃላፊነቶች እና ግጭቶችም ሊነሱባቸዉ ይችላሉ።

የግልግል ስምምነት ወሰኑ የትኞችን ወገኖችን እንደሚያካትት በተቻለ መጠን በግልፅ መቀመጥ አለበት። በተለይ ባለ ብዙ ወገን ተዋዋይ ወገኖች ሲኖሩ ለምሳሌ፡- የግንባታ ዉል ሲደረግ ንዑስ ተዋዋይ ወገኖች ቀላል የማይባል ድርሻ ይኖራቸዋል። በተመሳሳይም የስራዉ ባለቤት ለብቻዉ ከአማካሪ ድርጅት የሚገቧቸዉ ዉሎች ስራዉን ፋይናንስ ከሚያደርጉ ተቋማት ጋር የሚገቡ ዉሎች ወይም በዋናዉ ዉል አፈፃፀም ላይ የሚነሱ የሙያተኛን ዉሳኔ የሚሹ ጉዳዮች በግልግል ዳኝነቱ የሚሰጣቸዉ እዉቅና ሁሉ በደንብ ታስቦበት በግልግል ስምምነቱ መገለፅ አለበት።

ሌላኛዉ የግልግል ዳኝነት ወሰኑን በተመለከተ ትኩረት የሚሻዉ ምን ምን ጉዳዮች ናቸዉ በግልግል ዳኝነቱ ሊፈቱ የሚችሉት የሚለዉም ጥቅምን በሚያስከብር መልኩ ሊገደብ ይገባል።በጣም ተለምዶአዊ የሆነዉ የግልግል ስምምነቱ የሚፈታዉን ግጭት ለመወሰን የምንጠቀምበት አረፍተ ነገር "ከዚህ ዉል ጋር በተያያዘ፣ የሚነሱ ማናቸዉም ግጭቶች በግልግል ስምምነት ሊወሰን ይችላል።" (parties may refer to arbitration “all or certain disputes which have arisen or which may arise between them) ነገር ግን የዚህ አይነት ትኩረት ሳይሰጣቸዉ የሚገቡ ሀረጎች ብዙ መዘዝ ወይም በግልግል ስምምነት እንዲታዩልን የማንፈልጋቸዉን ጉዳዮች ጎትቶ ወደ ግልግል ዳኝነት ሊያስገባቸዉ ይችላል። ስለሆነም ከዉሉ ጋር የሚያያዙ ነገር ግን ለግልግል ዳኝነት እንዲቀርቡ የማይፈለጉ ነገሮችን ለይተን ከግልግል ዳኝነት ስምምነት ወሰኑ ማዉጣት ይመረጣል። ለምሳሌ፡- በአንድ የመድሃኒት ግዢ የመድሃኒቱን ደረጃ የማሟላት ጉዳይ ላይ የሚነሱ አለመግባባቶች የመድሃኒቱን ግዢ በሚያከናዉነዉ ሀገር ፍርድ ቤት ብቻ ወይም የደረጃ መዳቢ መስሪያ ቤት እንዲወሰን ሊደረግ ይችላል።

የግልግል ስምምነቱ ከምንገባዉ ወገን ጋር የይቻቻልልን ጥያቄ እና የተከሳሽ ከሳሽነት ጉዳዮችም ሊነሱ ስለሚችሉ በግልግሉ መግባቱ ምን ሊያስከትልብን እንደሚችል በቂ የዳሰሳ ጥናት ሊደረግ ይገባል። በተቋም በሚደረጉ የግልግል ዳኝነቶች አንደ ተቋሞች ሁኔታ የግልግል ዳኝነቱ ስምምነት ፈራሚ ያልሆኑ ሌሎች ሶስተኛ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ዉሳኔዉ ጥቅማቸዉን ሊጎዳባቸዉ እንደሚችሉ በመግለፅ ወደ ግልግል ዳኝነቱ ሊገቡ ስለሚችሉ እነዚህም ታሳቢ ለደረጉ ይገባል። በአንድ የግልግል ዳኝነት ለአንደኛዉ ተገላጋይ ወገን ዋስትና የሰጠን ሰዉ የግልግል ስምምነቱ ፈራሚ ሳይሆን እንደ ተዋዋይ ተቆጥሮ ዉሳኔ አርፎበት እናያለን። ዞሮ ዞሮ ይህ ዉሳኔ በፍርድ ቤት ሳይፈፀም ቀርቷል። ነገር ግን አንዳንዴ በግልግል ስምምነቱ የሚገዙ ወገኖችን መግለፁ ብቻ በቂ አይሆንም። የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ የሚገዛበት ህግም በአስገዳጅነት ሌሎች ፈራሚ ያልሆኑ ወገኖች እንዲገቡ ፈቃጅ ሊሆን ይችላል።

የፍርድ ቤቱ ዉሳኔ እንደሚከተለዉ ተቀምጧል፡-

39. A court ruled that an arbitration agreement contained in a contract was not automatically binding in relation to a guarantor to the extent the guarantor was not a party to the said agreement and its obligations were independentfrom the principal agreement.683 (uNCITRAL 2012 Digest of Case Law on the Model Law on International Commercial Arbitration) የአብዛኛዉ ሀገር የግልግል ዳኝነት ህግ ፈራሚ ያልሆኑ ወገኖች ወደ ግልግሉ የሚገበቡበትን ሁኔታ በዝምታ ያልፋታል። ነገር ግን አንዳንድ ሀገሮች(ኔዘርላንድ፣ ሩስያ) ቀጥሎ እንደተቀመጠዉ የግልግል ስምምነት ፈራሚ ያልሆኑ ሶስተኛ ወገኖች ወደ ግልግሉ የሚገቡበትን ሁኔታ ደንግገዋል። የዚህ አይነት ህግ መኖሩ የግልግሉን ስምምነት ተፈፃሚነት እድል ስለሚያሰፋ ጥሩ ነዉ።

"Article 1045 of the Netherlands Arbitration Act (1523) allows a third party who has an interest in the outcome of the arbitral proceedings to request to join the proceedings, or to intervene therein. Similarly, a party who claims to be indemnified by a third party may also serve a notice of joinder on such a party. In any of these cases joinder or intervention will only be granted by the arbitrators if the third party consents in writing to the arbitration agreement."

Article 7 of the Russian Arbitration Act (1524) allows joinder of non signatories to arbitral proceedings only upon express consent of all involved parties, including the non signatory itself.

በዚህ ጉዳይ ላይ ICC መጣመርን የሚከለክል የነበረ ሲሆን አሁን ግን ይህ ተቋም ሶስተኛ ወገኖች በተቀመጡ መስፈርቶች መሰረት ወደ ግልግሉ የሚገቡበት ሁኔታ ፈጥሯል። ነገር ግን አሁንም በህጋቸዉ አላካተቱትም በአሰራር እንጅ፡-

"The ICC Rules (1543) :

The ICC rules include no direct provision on the joiner of third parties to arbitration proceedings. Traditionally, the ICC rules have been viewed as one of the most restrictive page "568" for the extension of the arbitral clause to third parties. Parties to arbitration seemed to be restricted to those named in the original request for arbitration in application of article 4.3 of the ICC Rules, which imposes that the request identifies the parties. Under this doctrine, it was exclusively for the claimant to determine the parties to the arbitration. This position was deeply criticised by many, arguing that granting the claimant alone with the right to decide on the subjective configuration of the arbitration violated the parties' right to equal treatment (1544) .

However in recent years the ICC's strict position seems to have evolve and loosen up, and as reported by Ms. Anne Marie Whitesell and Mr Eduardo Silva Romero (1545) the ICC has begun to accept joinder of parties in ICC arbitrations in two scenarios:

• Prima facie decisions: In cases of request for arbitration filed against several respondents, some of which were not signatories to the agreement, the ICC via article 6(2) has prima facie considered them parties to the arbitration when one of the theories to allow the joinder of third parties concurred. (1546)

• Third parties included upon the instance of respondents: The ICC permits respondents to join additional parties if three cumulative conditions are met (i) the additional party must have signed the arbitration agreement: (ii) the respondent must raise claims against the new party; and (iii) the new party must be joined before the arbitral tribunal has been conformed or,  alternatively must consent to any existing tribunal."

## 2. የግልግል ዳኝነቱ የሚመራበት የግልግል ዳኝነት ህግ መምረጥ

የግልግል ዳኝነቱ የሚመራበት ህግ በምን መስፈርት መምረጥ አለበት?

መነሻ፡-በግልግል ዳኝነት ስምምነቱ መሰረት ተዋዋይ ወገኖች በመረጡት የግልግል ህግ ማለትም  የመቀመጫዉን አስገዳጅ  ህግ እንደተጠበቀ ሆኖ ወይም የግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫ የሆነዉ ሀገር የግልግል ህግ መሆን ስለሚችል የነዚህን ልዩነቶች ባላቸዉ ጥቅም በመመንዘር ገዢዉ ህግ ሊመረጥ ይገባል።

የግልግል ዳኝነት ስምምነት ለማድረግ ከተወሰነ በኋላ የግልግል ዳኝነቱ የሚመራበትን ህግ መርጦ መወሰኑ ቀዳሚዉና በግልግል ዳኝነቱ ሂደት ላይ ሁንተናዊ ተፅዕኖ አለዉ። ተዋዋይ ወገኖች ስምምነታቸዉን የሚገዛዉን ህግ ከመምረጣቸዉ በፊት የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ ይህንን የመምረጥ መብት ለተዋዋይ ወገኖች የሚሰጥ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ የሚተዳደርበት ህግ ቢመረጥም ግን የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ የሆነዉ ሀገር የሚጠቀምበት የግልግል ህግ ወደ ጎን የማይባልባቸዉ ነጥቦች አሉ። በዋናነት የተዋዋይ ወገኖችን የመዋዋል ችሎታ፣ ስምምነቱ የሚፀና መሆን አለመሆኑን፣ ጉዳዩ ለግልግል የሚበቃ መሆን አለመሆኑን፣ እና ሊታለፉ የማይችሉ ስነስርዓታዊ ፍትህ(procedural due process of law) የሚመለከቱ የመቀመጫዉ ህጎች በአስገዳጅነት የሚሰሩ ይሆናሉ። እነዚህን ድንጋጌዎች ችላ ማለት የግልግል ዳኝነቱን ፈራሽ ሊያስደርገዉ እና ተፈፃሚነት እንዳይኖረዉ ሊያደርግ ይችላል። የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ የሚገዘበት ህግ በተዋዋይ ወገኖች ቢመረጠም ወይም የመቀመጫዉ ሀገር ህግ የሚገዛዉ ቢሆንም በየትኛዉም አማራጭ የፀና መሆን የሚችል መሆኑን ቀድመን ማረጋገጡ የግልግል ሂደቱ በአጭሩ እንዳይቀጭ ይታደግልናል።

በግልግል ዳኝነት ህግ መረጣ ላይ ከሀገራት የግልግል ዳኝነት ህግ በተጨማሪ የግልግል ዳኝነት ተቋማት ጉዳዮን እንዲያዩ በተመረጡ ግዜ ተቋማዊ ህጎችም በአስገዳጅነት ወይም በአማራጫነት ተፈፃሚነት ሊኖራቸዉ ስለሚችል የነዚህን ህጎች ተፅዕኖም አስቀድሞ ማወቅ ያሻል። የግልግል ዳኝነት ተቋማት ጉዳዩን እንዲወስኑና የራሳቸዉን ህግ በሂደቱ እንዲፈፅሙ በስምምነቱ ሲገለፅ አስገዳጅ ያልሆኑ የግልግል ዳኝነቱን መቀመጫ የግልግል ህግ ተክተዉ የሚሰሩ ይሆናሉ። አንዳንድ የግልግል ዳኝነት ተቋማትን የግልግል ዳኝነት ህግ መምረጥ በራሱ የግልግል ዳኝነት ተቋሙን ጉዳዮን እንዲወስን እንደመምረጥ የሚቆጠር ነዉ። የተቋማት የግልግል ህግ በአብዛኛዉ በተቋሙ የዳኝነት አስተዳደርን እና ስነ ስርዓታዊ ጉዳዮችን የሚወስን ከመሆኑ አንፃር ህጉን የመምረጥ ነገር ተቋሙን እንደመምረጥ የሚቆጠር ነዉ።

ቀጥሎ የተቀመጡት የ ICC እና LCIA አንቀፆች ከላይ ያወራነዉን ያሳዩናል።

ICC rules article 6(2)፡- " By agreeing to arbitration under the Rules, the parties have accepted that the arbitration shall be administered by the Court. "3) LCIA Article 16 Seat(s) of Arbitration and Place(s) of Hearing "16.1. The parties may agree in writing the seat (or legal place) of their arbitration at any time before the formation of the Arbitral Tribunal and, after such formation, with the prior written consent of the Arbitral Tribunal. 16.2 In default of any such agreement, the seat of the arbitration shall be London (England), unless and until the Arbitral Tribunal orders, in view of the circumstances and after having given the parties a reasonable opportunity to make written comments to the Arbitral Tribunal, that another arbitral seat is more appropriate. Such default seat shall not be considered as a relevant circumstance by the LCIA Court in appointing any arbitrators under Articles 5,9A,9B,9C and 11.16.3 The Arbitral Tribunal may hold any hearing at any convenient geographical

place in consultation with the parties and hold its deliberations at any geographical place of its own choice; and if such place(s) should be elsewhere than the seat of the arbitration, the arbitration shall nonetheless be treated for all purposes as an arbitration conducted at the arbitral seat and any order or award as having been made at that seat. 16.4 The law applicable to the Arbitration Agreement and the arbitration shall be the law applicable at the seat of the arbitration, unless and to the extent that the parties have agreed in writing on the application of other laws or rules of law and such agreement is not prohibited by the law applicable at the arbitral seat."

ሀገራት ያላቸዉ የአለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ህግ ልዩነቶች የሚወጡለት ነዉ። ከላይ እንደተገለፀዉ የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ ህግ የግልግል ዳኝነቱን ስምምነት የሚገዛዉን ህግ ተዋዋይ ወገኖች መምረጥ እንደሚችሉ ከፈቀደ የተመረጠዉ የግልግል ዳኝነት ህግ የሚከተሉትን ነገሮች ስለሚወስን ገዢ ህጉ ቀጥሎ በተዘረዘሩ ነጥቦች ላይ ያለዉን አቋም ማወቅ ያስፈልገናል፡-

1. የግልግል ዳኝነቱ የሚመራበት ህግ የግልግል ዳኝነቱን ስምምነት የፀና መሆን አለመሆን ይወስናል። የግልግል ዳኝነት ስምምነት የሚመራበት ህግ በግልግል ሊፈታ የታሰበዉ ግጭት ላይ ከሚፈፀመዉ ህግ የተለየ የመሆን እድል አለዉ፤ ይሆናልም። (የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ከዋናዉ ዉል ተነጣጥሎ የሚታይ መሆኑ የግልግል ዳኝነት መርህ ነዉ። the principle of severability/ separability.) የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ/ቦታ ያለዉ የግልግል ህግ ለተዋዋይ ወገኖች ይህንን ህግ የመምረጥ ነፃነት የሚሰጥ ከሆነ በዚሁ ህግ በስምምነት መወሰን ካልቻሉ ደግሞ የግልግል ስምምነቱን መፅናት የሚወሰነዉ በግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ ህግ መሰረት ይወሰናል። ለምሳሌ ያህል የሲዊዘርላንድ አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ህግ መቀመጫዉን በዚያ ያደረገ ግልግል ተዋዋይ ወገኖች በመረጡት ህግ ስምምነታቸዉ የፀና መሆን አለመሆኑን ማስወሰን እንደሚችሉ ፈቃጅነት አለዉ።

የሲዊዘርላንድ ህግ የሚከተለዉን ይላል፡-

‘‘Article 178

III. Arbitration agreement

1. The arbitration agreement must be made in writing, by telegram, telex, telecopier or any other means of communication which permits it to be evidenced by a text.

2. Furthermore, an arbitration agreement is valid if it conforms either to the law chosen by the parties, or to the law governing the subject-matter of the dispute, in particular the main contract, or to Swiss law.

3. The arbitration agreement cannot be contested on the grounds that the main contract is not valid or that the arbitration agreement concerns a dispute which had not as yet arisen‘‘

2. ተከራካሪ ወገኖች በሂደቱ ሊኖራቸዉ ስለሚችዉ የነፃነት ወሰን ገደብን ያስቀምጣል፡-

2.1.የግልግል ዳኝነቱ የሚመራበትን ህግ ለመምረጥ ያላቸዉ ነፃነት፣ የግልግል ዳኝነቱን ህጋዊ መቀመጫ ለመምረጥ ያላቸዉን መብት

2.2.የግልግል ዳኞችን የመምረጥ መብትን፣ በተለይ የተቋም ህግ ሲመረጥ....ዳኞችን ለመምረጥ ያለዉ መብት፣ በህጉ ዳኛ መሆን ማን እንደሚችል ለመገደብ የተደረጉ ገደቦች፤ለምሳሌ፡- የዳኛዉን ዜግነት የተመለከቱ ጉዳዮች የሚመረጡ ዳኞችን ሊወስን ይችላል።.

2.3.ተከራካሪ ወገኖች በዳኞች ላይ ሊያነሱ ስለሚችሉት የይነሳልኝ ተቃዉሞ መብት

2.4.በግልግል ዳኝነቱ ሂደት የግልግል ጉባኤዉ ወይም ዳኛዉ ወይም በመቀመጫዉ ያለዉ ፍርድ ቤት ግዚያዊ ትዕዛዝ ለመስጠት ያለዉ ስልጣን

2.5.በመቀመጫዉ ያለዉ ፍርድ ቤት ዳኞች ባልተሾሙ ግዜ ለመሾም ያለዉ ስልጣን፣ ምስክሮችን እና ሌሎች ባለሙያዎችን እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ለመስጠት ያለዉ ስልጣን

2.6.በዉሳኔዉ ላይ ይግባኝ የማለት እና ፈራሽ ለማድረግ የሚደረጉ የመብት ጥያቄዎችን

2.7.ጉዳያቸዉን ጉባኤዉ ባደረጉት ስምምት መሰረት እንዲወስንላቸዉ ለማስደረግ ያላቸዉ መብት፤ ለምሳሌ፡- ፍርድ ቤቶች በረባ ባልረባ ጣልቃ እንዳይገቡ የሚከለክል ህግ መኖሩን ማረጋጥ፣ ፍርድ ቤቶች ለግልግል ጉባዔዉ የሚሰጡትን ድጋፍ በተመለከተ ሊሆን ይችላል

2.8.በክርክሩ ሂደት ሊተገበሩ ስለሚችሉ መሰረታዊ ህጎችን እና ስነ ስርዓት ህጎችን ተከራካሪ ወገኖች የመምረጥ ነፃነቶች ገዳቢ ወይም ፈቃጅ ሊሆን ይችላል።

**3.** የግልግል ዳኝነቱ ዳኞች/ የግልግል ዳኝነት ተቋም መረጣ

ሌላዉ በስምምነቱ ተኩረት ሊሰጠዉ የሚገባዉ የግልግል ዳኝነት ጉዳዔዉን የሚመለከት ነዉ። ግዚያዊ የግልግል ጉባዔ (adhoc arbitration) ይቋቋም ወይስ የግልግል ዳኝነት ተቋም (institutional arbitration) ይመረጥ የሚለዉ የመጀሪያዉ ነጥብ ሆኖ ከነዚህ ዉስጥስ የትኛዉ ይሁን የሚለዉም ዋና ጉዳይ ነዉ። ሁለቱም አይነት ግልግሎች በእጅጉ የተለየዩ ስለሆነና የግልግሉ ሂደት እና ዉጤታማነት ላይ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር እያንዳንዳቸዉ ሊሰጡን የሚችሉትን ጥቅሞች መመዘን አለብን።

ከዚህ በታች ያለዉ ፅሁፍ ከጥቅም አንፃር በሁለቱ መካከል ያለዉን ልዩነት ያሳየናል።

‘‘Based on the nature of the arbitral tribunal that is assigned to resolve the dispute, arbitration can be classified as ‘ad hoc’ and ‘institutional arbitration’. Parties are the one who determine the type of the arbitration under the arbitration agreement. Ad hoc arbitration is where parties manage the entire process themselves including the terms of appointment of the arbitrators and the basis on which the proceedings are to be conducted. In institutional arbitration the management of the case is handled entirely by the institution. Unlike ‘institutional arbitration’, the tribunal is formed only for a particular purpose and parties are completely free to adopt particulars of the proceeding. It is more flexible and less costly since parties can avoid institutional fees and bargain fees to arbitrators.

However, institutional arbitration is a type of an arbitration that took place in a certain arbitration institution. In institutional arbitration, proceedings of the arbitration are in accordance with the rules of the institution. This form of arbitration is popular among international commercial parties. Because parties believe that institutions are more experienced in effective administration of the proceeding and quality awards. It is obvious that high quality of the award increases enforceability of the award and benefits parties. There are many arbitration centers in every corner of the world. The well known arbitration institutions include: the International Chamber of Commerce (ICC), the American Arbitration Association (AAA), the Stockholm Chamber of Commerce, and the London Court of International Arbitration (LCIA).90‘‘

በግልግል ስምምነታችን ግልግሉን እንዲያየዉ ከግዚያዊ ጉባዔ ይልቅ የግልግል ተቋማትን የምንመርጥ ከሆነ ከተቋማት መካከል ስንመርጥ ደግሞ የሚከተሉትን መመዘን አለብን። ከገለልተኝነት፣ ከዉሳኔ ጥራታቸዉ፣ ቅልጥፍናቸዉ፣ የሚያስከፍት ዋጋ እንዲሁም የግልግል ዳኝነት ተቋሙ ያለዉ አለም አቀፋዊ ተቀባይነትና ልምድ አንፃር መመዘን ይኖርብናል። በተለይ ተቋሙ ያለዉ አቀፋዊ ተቀባይነትና ልምድ የዉሳኔዉ ተፈፃሚነት ላይ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር እንደ ጥቅም ሊወሰድ ይገባል።

በግልግል ተቋማት ዉስጣዊ አሰራሮች ሊኖሩ የሚችሉ ተፅዕኖዎች፡- ተቋማዊ የግልግል ዳኝነት ሲሆን ተከራካሪ ወገኖች በአስገዳጅነት የተቋሙን ህግ የሚጠቀሙ ከሆነ ዳኞችን የመምረጥ፣ ዳኞች ላይ ተቃዉሞ የማቅረብ መብትን እና መሰረቶችን፣ የማስረጃ አሰማምን ምዘናን፣ በዉሳኔዉ ላይ ያለን ዉስጣዊ የይግባኝ ስርዓት፣ የግልግል ዳኝነት ተቋሙ በግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ዉስጥ ፈራሚ ላልሆኑ ሶስተኛ ወገኖች በግልግሉ ለመሳተፍ መቻል የሚችሉ ወይም የማይችሉ መሆኑን፣ ስለማቻቻል እና የተከሳሽነት ክሶችን ወዘተ በነፃነት የመወሰን ነገር ከተከራካሪ ወገኖች ሊወስዱ ወይም ተከራካሪ ወገኖች ሊወስኑ የሚችሉበትን አግባብ ሊያስቀምጡ ይችላሉ።

ከላይ ያሉ እንደ ጥቅም ሊወሰዱ የሚችሉ ነገሮች እንደተጠበቁ ሁነዉ ሌሎች ተፅዕኖዎችም እንዳሉት አይዘነጋም። ሌሎች በተቋም መረጣ ሊመጡ የሚችሉ ተፅዕኖዎች በህግ መረጣ እና በጉባዔዉ መቀመጫ መረጣ ሊያስከትለዉ ከሚችለዉ ተፅዕኖ ጋር ተመሳሳይነት ስላለዉ አንባቢዉ እነዚህን ጉዳዮች በዚህ ጽሑፍ ሌላኛዉ ክፍል ከተቋም ጋር እያገናኘ እንዲመለከታቸዉ ይመከራል።

ቀጥሎ የ ICC እና LCIA የግልግል ተቋማት በዚህ ዙሪያ ሊነሱባቸዉ የሚችሉትን ነጥቦች እንመልከት፡-

3.1. ICC የሚባለዉን ተቋም መምረጥ የግልግል ዳኝነቱን ነገር የማስተዳደር እንጅ እራሱ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ስላለመሆኑ ዳኞችን የመምረጥ፣ የመቃወም ወይም ሌሌች ተያያዥ ጉዳዮችን በጉባዔዉ ላይ ማቅረብ እንደሚቻል እና ተቋሙም ከፍርድ ቤቱ ቀድሞ እነዚህን ጉዳዮች የማየት ስልጣን እንዳለዉም እንረደዳለን። (ለምሳሌ የተሰጠዉን ዉሳኔ የማፅደቅ ስራ)

ቀጥሎ ያለዉ ጽሁፍ የሚከተለዉን ያመለክተናል፡

International Court of Arbitration፡ The International Court of Arbitration (the1)“Court”) of the International Chamber of Commerce (the “ICC”) is the independent arbitration body of the ICC. The statutes of the Court are set forth in Appendix I.The Court does not itself2) resolve disputes. It administers the resolution of disputes by arbitral tribunals, in accordance with the Rules of Arbitration of the ICC (the “Rules”). The Court is the only body authorized to administer arbitrations under the Rules, including the scrutiny and approval of awards rendered in accordance with the Rules. It draws up its own internal rules, which are set forth in Appendix II (the “Internal Rules”)

3.2.በአንዳንድ የግልግል ተቋማት የተለያዩ የግልግል ዳኝነት መዝገቦችን እንዲጣመሩ ማድረግ እንደሚቻል፡-

ለምሳሌ፡- ተዋዋይ ወገኖች በግልግል ዳኝነት ጉዳያቸዉ እየታየበት ያለበት ተቋም ካለ እና አሁን ደግሞ የግልግል ስምምነት ያደረጉበት ጉዳዩ ቀድሞ ከነበረዉ መዝገብ ላይ መጣመር ከቻለ እነዚህን አይነት ተቋሞች መምረጥ ተገቢ ይሆናል። ICC ህግ……

Article 10: Consolidation of Arbitrations The Court may, at the request of a party, consolidate two or more arbitrations pending under the Rules into a single arbitration, where: the parties a)have agreed to consolidation; or all of the claims in the arbitrations are made under the same b)arbitration agreement; or where the claims in the arbitrations are made under more than one c) arbitration agreement, the arbitrations are between the same parties, the disputes in the arbitrations arise in connection with the same legal relationship, and the Court finds the arbitration agreements to be compatible, deciding whether to consolidate, the Court may take into accountInany circumstances it considers to be relevant, including whether one

or more arbitrators have been confirmed or appointed in more than one of the arbitrations and, if so, whether the same or different persons have been confirmed or appointed. When arbitrations are consolidated, they shall be consolidated into the arbitration that commenced first, unless otherwise agreed by all parties…………………

3.1.

3.3.

No party or third person may appoint any arbitrator under the arbitration Agreement: the LCIA Court alone is empowered to appoint arbitrators (albeit taking into account any written agreement or joint nomination by the parties).5.8 A sole arbitrator shall be appointed unless the parties have agreed in writing otherwise or if the LCIA Court determines that in the circumstances a three---member tribunal is appropriate (or,exceptionally,more than three).5.9 The LCIA Court shall appoint arbitrators with due regard for any particular method or criteria of selection agreed in writing by the parties.

The LCIA Court shall also take into account the transaction(s) at issue, the nature and circumstances of the dispute, its monetary amount or value, the location and languages of the parties, the number of parties and all other factors which it may consider relevant in the circumstances.

3.4.

ሂደቱን ቀልጣፋ ለማድረግ በተቋማት በተጨማሪም ሌሎች የግልግል ዳኝነት የተቀመጡ ህጎችንም ማግኘት እንችላለን::: LCIA ህግ የግልግል ዳኝነት ዳኞችን ለመሾም የሚችለዉ ተቋሙ ብቻ ስለመሆኑ፤ ዳኞችን ለመሾም በተቋሙ የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን (እንደ ሚስጥራዊነቱን መጠበቅ) እና አንድ ዳኛ ይሁን ወይስ ሶስት የሚለዉ ስለሚወሰንበት አግባብ፦

**ICC** ህግ……

Article 22: Conduct of the Arbitration፥ The arbitral tribunal and the parties shall make every 1)effort to conduct the arbitration in an expeditious and cost-effective manner, having regard to the complexity and value of the dispute. In order to ensure effective case management, the arbitral 2) tribunal, after consulting the parties, may adopt such procedural measures as it considers appropriate, provided that they are not contrary to any agreement of the parties. Upon the request of any party, 3) the arbitral tribunal may make orders concerning the confidentiality of the arbitration proceedings or of any other matters in connection with the arbitration and may take measures for protecting trade secrets and confidential information. 4) In all cases, the arbitral tribunal shall act fairly and impartially and ensure that each party has a reasonable opportunity to present its case. The parties undertake to comply with any order made by the arbitral tribunal.5)

3.5.

በተጨማሪ የለንደኑ ተቋም የቃል ክርክር ሳይኖር በሰነድ ብቻ ጉዳያቸዉ እንዲሰማላቸዉ መስማማትን ይፈቅዳል፡-

## Article 19 Oral Hearing(s)

19.1 Any party has the right to a hearing before the Arbitral Tribunal on the parties' dispute at any appropriate stage of the arbitration (as decided by the Arbitral Tribunal), unless the parties have agreed in writing upon a documents---only arbitration. For this purpose, a hearing may consist of several part---hearings (as decided by the Arbitral Tribunal).

19.2 The Arbitral Tribunal shall organize the conduct of any hearing in advance, in consultation with the parties. The Arbitral Tribunal shall have the fullest authority under the Arbitration Agreement to establish the conduct of a hearing, including its date, form, content, procedure, time---limits and geographical place. As to form, a hearing may take place by video or telephone conference or in person (or a combination of all three). As to content, the Arbitral Tribunal may require the parties to address a list of specific questions or issues arising from the parties' dispute.

19.3 The Arbitral Tribunal shall give to the parties reasonable notice in writing of any hearing.

19.4 All hearings shall be held in private, unless the parties agree otherwise in writing.

## 4. የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ስልጣን በተመለከተ

የግልግል ዳኝነቱ የራሱን ስልጣን በራሱ ግዜ መወሰን የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ መኖሩን ማረጋገጥ የግልግሉን ቅልጥፍና የሚወስን ነዉ። በብዙ ሀገር ህጎች የጉባኤዉ ስልጣን የግልግል ዳኝነት ስምምነቱን የፀና መሆን አለመሆንን፣ በስልጣናቸዉ ለመወሰን ስለሚቻላቸዉ የፍሬ ነገር፣ ዳኞች ለማንሳት የሚደረግን ተቃዉሞ የመወሰን ነገሮችን ያካትታል። የጉባኤዉን ስልጣን በመቃወም ለፍርድ ቤት ጎን ጎን የሚሄድ ተመሳሳይ ነገር ሳያግዳቸዉ ዉሳኔ መስጠት መቻልን ሁሉ ያካትታል። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የግልግል ዳኝነት ህጎች ግን ለጉባኤዉ የሚሰጡት ስልጣን በግልግል ዳኝነቱ ስምምነት የፀና መሆን አለመሆን የመወሰንን ጉዳይ አያካትትም። የግልግል ዳኝነት ስልጣንን በራሱ ግዜ የመወሰን ነገር ጎን ለጎን ፍርድ ቤቶችንም ካለ አግባብ በግልግል ሂደቱ ጣልቃ የሚገቡበትን መንገዶች ሁሉ መገደብን እና ግልግል ዳኝነት ስምምነት ዉስጥ የሚወድቁ ጉዳዮችን ከማየት የሚከለክል ነዉ።

የግልግል ዳኝነቱ ጉባኤ ስልጣኑን መሰረት ተደርጎ ለሚነሱ የተዋዋይ ወገኖች ተቃዉሞ በራሱ ለመወሰን ያለዉ ስልጣን በተመለከተ የጀርመን ህግ ከኢትዮጵያ ህግ በተቃራኒዉ ምሉዕ የሚባል ስልጣን ለጉባኤዉ የሚሰጥ ነዉ።

የጀርመን ሀገር የግልግል ዳኝነት ህግ እንደሚከተለዉ ይነበባል፡-

"Section 1040 Competence of arbitral tribunal to rule on its jurisdiction

(1) The arbitral tribunal may rule on its own jurisdiction and in this connection on the existence or validity of the arbitration agreement. For that purpose, an arbitration clause which forms part of a contract shall be treated as an agreement independent of the other terms of the contract.

(2) A plea that the arbitral tribunal does not have jurisdiction shall be raised not later than the submission of the statement of defence. A party is not precluded from raising such a plea by the fact that he has appointed, or participated in the appointment of, an arbitrator. A plea that the arbitral tribunal is exceeding the scope of its authority shall be raised as soon as the matter alleged to be beyond the scope of its authority is raised during the arbitral proceedings. The arbitral tribunal may, in either case, admit a later plea if it considers that the party has justified the delay.

(3) If the arbitral tribunal considers that it has jurisdiction, it rules on a plea referred to in subsection 2 of this section in general by means of a preliminary ruling. In this case, any party may request, within one month after having received written notice of that ruling, the court to decide the matter. While such a request is pending, the arbitral tribunal may continue the arbitral proceedings and make an award."

የግልግል ጉባዔዉ ጉዳዮን በግልግል ለማየት በሚያደርገዉ ሂደት ስልጣኑን አስመልክቶ ለሚነሳበት ተቃዉሞ በራሱ የመወሰን ስልጣን በህጉ ከመስጠት አልፎ የጀርመን ህግ ፍርድ ቤቶችንም በግልግል ስምምነት የተካተተን ጉዳይ ከማየት ይከለክላቸዋል።

"Section 1032 Arbitration agreement and substantive claim before court "

(1) A court before which an action is brought in a matter which is the subject of an arbitration agreement shall, if the respondent raises an objection prior to the beginning of the oral hearing on the substance of the dispute, reject the action as inadmissible unless the court finds that the arbitration agreement is null and void, inoperative or incapable of being performed.

(2) Prior to the constitution of the arbitral tribunal, an application may be made to the court to determine whether or not arbitration is admissible.

(3) Where an action or application referred to in subsection 1 or 2 has been brought, arbitral proceedings may nevertheless be commenced or continued, and an arbitral award may be made, while the issue is pending before the court."

በተጨማሪም የጀርመን ህግ ፍርድ ቤቶች በግልግል ዳኝነት ሂደቱ ጣልቃ የሚገቡት በተፈቀደ ህጋዊ ምክንያት ብቻ እንደሆነ ይገልፃል። ይህ ማለት ፍርድ ቤቶች በረባ ባልረባ ወደ ግልግል ሂደቱ ጣልቃ እየገቡ እክል እንዳይፈጥሩ የሚረዳ እና ከመጀመሪያዉም የግልግል ዳኝነት የተመረጠበትን አላማ ለማሳካት የሚያስችል ነዉ።

እንደሚከተለዉ ይነበባል፡-

"Section 1026 Extent of court intervention"

In matters governed by sections 1025 to 1061, no court shall intervene except where so provided in this Book."

## 5. የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ

የግልግል ዳኝነቱ በተዋዋይ ወገኖች ባልተወሰነ ግዜ እና ተዋዋይ ወገኖች ዳኞችን ወይም ጉባኤዉን ማቋቋም ሳይቻል ተዋዋይ ወገኖች ለየትኛዉ ሀገር ፍርድ ቤት አመልክተዉ ዳኛ ማሾም ይችላሉ?

መነሻ፡- ቀድሞ የግልግል ዳኝነት መቀመጫዉን አለመወሰን ግልግሉ እንዲቆምና መፈናፈኛ እንዲያጣ ሊያደርግ ስለሚችል በግልግል ስምምነቱ ቀድሞ መወሰን ከዚህ ችግር ለመዉጣት ወሳኝ ነዉ፡፡

አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ስምምነት በሚደረግበት ወቅት ዋነኛዉ ብዙ ፀጋዎች ወይም ጣጣዎች ሊያስከትል የሚችለዉ ግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫ ነዉ፡፡ ህጋዊ መቀመጫ ማለት የግልግል ዳኝነቱ ዉሳኔ ዜግነት የሚያገኝበት ነዉ፡፡ ማለትም በመደበኛ ፍርድ የሚሰጥ የፍርድ ዉሳኔ የየትኛዉ ሀገር መንግስት ፍርድ ቤት እንደሰጠዉ እንደሚገለፀዉ ሁሉ የግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫም ከዚህ በታች ለምናያቸዉ ጉዳዮች ወሳኝነት ስላለዉ የግድ መሰየም ያለበት ይሆናል ማለት ነዉ፡፡ በመሰረቱ ህጋዊ የግልግሉ መቀመጫ ቦታ የሚባለዉ እና በአካል ግልግሉ የሚካሔድበት ቦታ ምንም ግንኙነት የሌለዉ ስለመሆኑ ቀድመን ግንዛቤ ልንወስድበት የሚገባ ነዉ፡፡ በሳሊኒ ኮንስትራክሽን እና በአዲስ አበባ ዉሃ ስራዎች መካከል በተፈረመ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ህጋዊ መቀመጫ እና በአካል ስራዎች የሚሰሩበትን ቦታ በአግባቡ ካለመለየት ወይም እነዚህን ቦታዎች ለያይቶ በግልፅ አለማስቀመጥ በመጨረሻ የግልግል ዳኝነቱን ሂደት የአዲስ አበባ ዉሃ ስራዎች አቋርጦ እንዲወጣ ምክንያት ሆኗል፡፡

የግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫ በተከራካሪ ወገኖች ባልተወሰነ ግዜ ዳኞች ወይም ተቋሙ መቀመጫዉን ይመርጣል፡፡ ለምሳሌ፡- LCIA የግልግል ህግ በምናይበት ወቅት ተዋዋይ ወገኖች በስምምነታቸዉ መቀመጫዉን ያልወሰኑ ከሆነ እንደገና የመምረጥ እድሉን ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑንና ላልተፈለገ ዉጤት የሚዳርግ መሆኑን ሊያስገነዝበን ይችላል፡፡ የግልግል ዳኝነቱን መቀመጫ በተዋዋይ ወገኖች በስምምነት ካልተወሰነ በአንዳንድ ተቋማት ህጎች ለግልግሉ የተቋቋመዉ ጉባዔ ካልፈቀደ ተዋዋይ ወገኖች የመምረጥ መብታቸዉን መልሰዉ ላያገኙት ይችላሉ፡፡ የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫም በስምምነቱ ያልተወሰ በሆነ ግዜ ሁሉ ተቋሙ ያለበት ሎንደን የግልግሉ መቀመጫ እንደሆነ የሚቆጠር መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

የ LCIA ህግ እንደሚከተለዉ ይነበባል፡-

"Article 16 Seat(s) of Arbitration and Place(s) of Hearing"

16.1 The parties may agree in writing the seat (or legal place) of their arbitration at any time before the formation of the Arbitral Tribunal and, after such formation, with the prior written consent of the Arbitral Tribunal. 16.2 In default of any such agreement, the seat of the arbitration shall be London (England), unless and until the Arbitral Tribunal orders, in view of the circumstances and after having given the parties a reasonable opportunity to make written comments to the Arbitral Tribunal, that another arbitral seat is more appropriate."

የግልግል ዳኝነቱ ቦታ በተዋዋይ ወገኖች ተመረጠም በጉባዔዉ የሚከተሉትን ነጥቦች ይወስናል፡-

- የግልግል ስምምነቱ በህግ ፊት የመፀና መሆኑን/ ሌላ መምረጥን ፈቃጅ ካልሆነ ምሳሌ የስዊዝ ህግ በተዋዋይ ወገኖች ወይም በፍርድ ቤት ዳኞች ሊሾሙበት/ ሊሻሩበት የሚችሉትበን ሂደት ይወስናል
- የሽምግልናዉ ጉባዔ ያለዉን ስልጣን በተመለከተ ለሚነሱ መቃወሚያዎች /
- የችሎቱን የስራ ቋንቋ የመጥሪያ እና ሌሎች በፍርድ ቤት የሚሰጡ ተያያዥ ነገሮችን ለምሳሌ፡- ምስክሮችን መጥራት እና ማስረጃ እንዲቀርብ ማዘዝ
- የእግድ እና ግዜያዊ ትዕዛዞችን የሚሰጥ ፍርድ ቤትን
- የመቀመጫዉ ፍርድ ቤት ስለሚኖረዉ ጣልቃ ገብነት
- መሰረታዊ ህጎች/ስነ ስርዓት ህጎች በተለይም አስገዳጅነት ያላቸዉን ህጎች በተመለከተ/ ሊታለፉ የማይችሉ የሀገሪቱን ብሔራዊ ፖሊሲ ጉዳዮች ይወስናል፤
- የግልግል ዉሳኔዉን ለማሻር መሰረት የሚሆኑ ነጥቦችን እና ዉሳኔዉን ለማሻር ለሚደረግ ማመልከቻ ስልጣን ያለዉ ፍርድ ቤት በመቀመጫዉ የሚገኘዉ ፍርድ ቤት ነዉ፤
- በግልግል ዳኝነት ዉሳኔዉ ላይ ቅር በመሰኘት ሊኖር ስለሚችል ይግባኝ የማየት ስልጣን የመቀመጫዉ ፍርድ ቤት ይሆናል

- የግልግል ዳኝነት ዉሳኔዉን ለማስፈጸም በሚደረግ ሂደት መቀመጫዉ ወሳኝነት አለዉ። በተለይም የግልግል ዳኝነቱ እንዲፈፀም አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት ከመቀመጫዉ ዉጭ ላለ ፍርድ ቤት ከሆነ ዉሳኔዉን ለመፈፀም የእንካ ለእንካ መርህን ለመተግበር ወይም አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነቶችን ለመፈፀም ስምምነት የገባ ሀገር ከሆነ ዉሳኔዉን ለመፈፀም ዉሳኔዉ የተገኘዉ በየትኛዉ ሀገር እንደሆነ እንዲያዉቅ፤ ምሳሌ፡- አንዳንድ ግዜ የግልግል ዳኝነቱን መቀመጫ በኢትዮጵያ በማድረግ ጥቅም ይገኝበታል በሚል የተሳሳተ እሳቤ የግልግል ዳኝነቱ ሊፈፀምባቸዉ የሚችሉ የሀገራትነ ብዛት ሲገድብ ይታያል። ዉሳኔዉን ለማስፈፀም ለፍርድ ቤት አቤቱታ ሲቀርብ አቤቱታዉ የቀረበዉ ግልግሉ የታየበት ሃገር ላለ ፍርድ ቤትም ይሁን ለሌላ ዉጭ ሀገር ላለ ፍርድ ቤት ዉሳኔዉ ከመፈፀሙ በፊት ሌላኛዉ ባለዕዳ የሚያነሳቸዉ መቃወሚያዎች የግልግል ዳኝነቱ የተቀመጠበትን ሀገር ህግ መሰረት የሚያደርጉ ናቸዉ።

## **6.** በግልግል ዳኝነቱ ተፈጻሚነት ስለሚኖራቸዉ መሰረታዊ እና የስነ ስርዓት ህጎች፡-

ተፈፃሚነት ያላቸዉ ህጎች ግልግሉ እንደሚመራበት ህግ (የግልግል መቀመጫዉ ሀገር ህግ፣ ግልግሉን በሚያየዉ ተቋም ህግ ወይም ግልግል ስምምነቱ እና ሂደቱ እንዲመራበት በተዋዋይ ወገኖች የተመረጠዉ ህግ) ፈቃጅነት በተከራካሪ ወገኖች ሊወሰኑ ይችላል። በዚህ ርዕስ ዉስጥ ተፈፃሚነት ያለዉ ህግ ስንል በግልግሉ ሊፈታ የታሰበዉን ግጭት ለመወሰን ተፈፃሚነት ያለዉን መሰረታዊ ህግ እና የግልግሉ ሂደት የሚመራበትን ስነ ስርዓታዊ ህግ ማለታችን ነዉ። በተለይ አሁን አሁን ላይ ያሉ አብዛኛዉ ዘመናዊ አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ህጎች በመሰረታዊ ጽንሰ ሃሳቦቻቸዉ የተከራካሪ ወገኖን ነፃነት አድማስ የሚያሰፉ እና በጉዳዩ ተፈፃሚነት የሚኖራቸዉን መሰረታዊ ህጎች (substantive laws) ወይም የግልግሉ ሂደት የሚመራበትን የስነ ስርዓት ህጎች (procedural laws) ተከራካሪ ወገኖች እንዲመርጡ እድል ይሰጣሉ።

*መሠረታዊ ህጎችን ተከራካሪ ወገኖች ስለመምረጣቸዉ፡-*

ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኞች ግጭቱን በሚወስኑ ግዜ በዋናዉ ዉል ላይ ተፈፃሚ ስለሚያደርጉት መሰረታዊ ህግ በግልግል ዳኝነት ስምምቱ ሊወስናሉ ይችላሉ። በአብዛኛዉ ተፈፃሚ እንዲሆን የሚመረጠዉ ህግ ምንም ገደብ ሳይደረግ ሊመረጥ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪም ህግ ያልሆኑ(non-principles of law/official laws) ርትዕ (ex et bono) ወይም የንግድ ማህበረሰቡ ልማዳዊ አሰራሮችን(lex mercatoria) ብቻ መሰረት አድርገዉ ዳኞች ጉዳዩን እንዲወስኑላቸዉ ለማድረግ ተዋዋይ ወገኖች በግልግል ስምምነቱ ሊያሰፍሩ ይቻላቸዋል። ይህ ሁሉ የሚሆነዉ ግን የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ የሚገዛበት ህግ ለተከራካሪ ወገኖች ይህንን የመምረጥ መብት የሚሰጥ ከሆነ ነዉ።( አከራካሪ ቢሆንም የኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት ህግ ተዋዋይ ወገኖች ጉዳያቸዉ በርትዕ (ex et bono) ወይም በንግድ ማህበረሰቡ ልማዳዊ አሰራሮች(lex mercatoria) እንዲወሰንላቸዉ መስማማት እንደሚችሉ አልተደነገገም። ተከራካሪ ወገኖች ባልመረጡ ግዜ የግልግል ዳኞች ተፈፃሚ የሚሆነዉን ህግ የሚወስኑ ይሆናል።

UNCITRAL model law ተዋዋይ ወገኖች ስላላቸዉ ነፃነት የሚከተለዉን ይላል፡-

Article 28. Rules applicable to substance of dispute

(1) The arbitral tribunal shall decide the dispute in accordance with such rules of law as are chosen by the parties as applicable to the substance of the dispute. Any designation of the law or legal system of a given State shall be construed, unless otherwise expressed, as directly referring to the substantive law of that State and not to its conflict of laws rules.

(2) Failing any designation by the parties, the arbitral tribunal shall apply the law determined by the conflict of laws rules which it considers applicable.

(3) The arbitral tribunal shall decide ex aequo et bono or as amiable com- positeur only if the parties have expressly authorized it to do so.

(4) In all cases, the arbitral tribunal shall decide in accordance with the terms of the contract and shall take into account the usages of the trade applicable to the transaction.

የእንግሊዝ ሀገር የግልግል ዳኝነት ህግም በሚከተለዉ መልኩ የተዋዋይ ወገኖችን ተፈፃሚ የሚሆነዉን መሰረታዊ ህግ የመምረጥ ነፃነት አስቀምጧል፡-(በብዙ የግልግል ተቋማት ህጎችም ይህ ነፃነት የተከበረ ነዉ)

‘‘46. Rules applicable to substance of dispute

1" The arbitral tribunal shall decide the dispute-

(a) in accordance with the law chosen by the parties as applicable to the substance of the dispute, or

(b) if the parties so agree, in accordance with such other considerations as are agreed by them or determined by the tribunal.

2" For this purpose the choice of the laws of a country shall be understood to refer to the substantive laws of that country and not its conflict of laws rules.

3" If or to the extent that there is no such choice or agreement, the tribunal shall apply the law determined by the conflict of laws rules which it considers applicable. ‘‘

ተከራካሪ ወገኖች መሰረታዊ ህጉን መምረጥ መቻላቸዉ የሚከተለዉን ጥቅም ይሰጣል፡- እንደዚህ አይነት ፈቃጅነት ያላቸዉን የግልግል ዳኝነት ህጎች (የግልግል ዳኝነቱን አስመልክቶ የሚነሱ ጉዳዮችን እንዲወስኑ የተመረጡ ህጎች) የተከራካሪ ወገኖችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የግልግል ዳኝነት እንዲኖር የሚያደርግ ነዉ፡፡ ለምሳሌ ተከራካሪ ወገኖች ያደረጉትን ዉል ተከትሎ ሊነሳ የሚችልን ግጭት ሁለቱም በሚያዉቁት ህግ ማለትም ተገማችነት ባለዉ ሁኔታ ግጭታቸዉን መፍታት ያስችላቸዋል፡፡

በተጨማሪም ተከራካሪ ወገኖች እንደገቡት ዉል ባህሪ የተሻለ የህግ ማዕቀፍ ኑኖት ዉላቸዉን በአሰቡት ሁኔታ ተፈፃሚነት እንዲኖረዉ ይረዳቸዋል፡፡ለምሳሌ፡- ኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉ ግንባታን የሚመለከቱ ህጎች ትኩረትን አግኝተዉ ያልዳበሩ እና ትልልቅ ፕሮጀክት ስራዎችን ለማስተዳደር ብቃት የሌላቸዉ ሁነዉ እናገኛቸዋለን፡፡ ስለዚህ፡- አለም አቀፍ የግንባታ ዉሎች ሲፈረሙ ዉሉን በተሻለ የሚያስተዳድረዉ የሌላ ሀገር ህግ ካለ መርጠን እሱን ብናደርግ ጠቃሚ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

ሌላዉ ከጠቀሜታዉ አንፃር ተዋዋይ ወገኖች በዉሉ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነዉን ህግ መምረጥ መቻላቸዉ በአለም አቀፍ የግል ህግ (principles of private international law) ግዜ የሚነሳዉን የህጎች ግጭት(conflicts of law) በማስወገድ ዉሳኔዉ በቅልጥፍና እንዲወሰን ለማስደረግ ይችላል፡፡ነገር ግን ከላይ የተገለፀዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በጉዳዩ ተፈፃሚነት እንዲኖረዉ የሚመረጠዉ ህግ አንዳንዴ ከጉዳዩ በጣም የራቀ በሆነ ግዜ ዉሳኔዉ እዉቅና ወይም በሚፈፀምበት ሀገር ተቃዉሞ እንዳይገጥመዉ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ ረገድ መሰረታዊ የሆኑ የአለም አቀፍ የግል ህግ መርሆች /principles of private international law/ ከግንዛቤ ሊገቡ ይገባል፡፡ ከነዚህ መርሆች ዉስጥም ተፈፃሚ የሚሆነዉ መሰረታዊ ህግ ከጉዳዩ ጋር እዉነተኛ የሆነ ቅርብ ግንኙነት እንዲኖረዉ የሚጠይቀዉ መርህ ተጠቃሽ ነዉ፡፡ በተከራካሪ ወገኖች የተመረጠዉ ህግ ለጉዳዩ ያለዉ ምክንያታዊ፣ እዉነተኛ ቅርበትና ግንኙነት ከግምት ሊገባ የሚገባ ወሳኝ ነገር ነዉ፡፡ ይህንን ችላ ማለት አልፎ አልፎ ዉሳኔዉን ፈራሽ በማድረግ ሂደት፣ እዉቅናና ተፈጻሚ በማስደረግ ሂደት እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

ለምሳሌ፡- ዋናዉ ዉል ላይ ሊተገበር በግልግል ስምምነቱ የተገለፀዉ ‘‘X‘‘ የተባለ የአፍጋኒስታን ኦፒየም አዘዋዋሪዎች ቡድን ዉስጠ ደንብ ቢሆን፣ የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ ደግሞ በእንግሊዝ ቢሆን፣ የተመረጠዉ ህግ በማስገደድ የተፈረመ ዉል ፈራሽ አይሆንም የሚል ቢሆን ይህንን መሰረት ተደርጎ የሚሰጠዉ ዉሳኔ በእንግሊዝ ፍርድ ቤቶች ከሀገሪቱ ፖሊሲ ጋር የሚቃረን ነዉ ተብሎ ፈራሽ ሊሆን ይችላል፡፡

ሥነ ሥርዓት ህጎችን ተከራካሪ ወገኖችን ስለመምረጣቸዉ፦

ካለይ እንደተገለፀዉ በተመሳሳይ መልኩ ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነቱ የሚመራበትን የስነ ስርዓት ህግ ሊመርጡ ይችላል። በእርግጥ የስነ ስርዓት ህግ ሲመረጥ መሰረታዊ ህግ መረጣ ላይ ካለዉ የጠበቡ ነፃነቶች ነዉ የሚኖራቸዉ። በዋናነት የግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫ የሆነዉ ሀገር የስነ ስርዓት ህጎች በአብዛኛዉ አስገዳጅነት ያላቸዉ ሁነዉ እናገኛቸዋለን። የግልግሉ መቀመጫ ሀገር ህጎች አንዳንድ ሊታለፉ የማይችሉ ሥነ ሥርዓታዊ ጉዳዮች (du process of law/ mandatory procedural rules of the seat/ በማንኛዉም ሁኔታ ሊታለፉ እንደማይችሉ ያስቀምጣሉ። የእነዚህ ሥነ ሥርዓታዊ ህጎች መጣስ የግልግል ዳኝነት ዉሳኔዉን ለመቃወሚያ መሰረት የሚሆኑ እና አለመከበራቸዉ ደግሞ ዉሳኔዉን የሚያሽሩ ናቸዉ።/setting aside of arbitral awards/. በአጠቃላይ ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኞች ግልግሉን የሚመሩበትን ስነ ስርዓት መምረጥ ትልቅ ጥቅም የሚሰጣቸዉና ቅልጥፍና በተሞላበት አኳኋን ጉዳያቸዉ ዉሳኔ እንዲያገኝ የሚያስችል ቢሆንም አስገዳጅ የሆኑ የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ ስነ ስርዓት ህጎች ወደ ጎን መባል የለባቸዉም። ይህንን አለማክበር ግን ዉሳኔዉ በተቃዉሞ እንዲፈርስ፣ እዉቅና እንዲነፈገዉ ወይም ተፈፃሚ እንዳይሆን ስለሚያደርግ ትልቅ ጥንቃቄ የሚሻ ነዉ።

ተዋዋይ ወገኖችን የግልግል ዳኝነት ሂደቱ የሚመራበትን ስነ ስርዓት ህግ የመምረጥን ነፃነት በተመለከተ የስዊዝ እና የጀርመን ህጎች እንደሚከተለዉ ያስቀምጡታል።

የስዊዝ ህግ፦

Article 182

VI. Procedure

1. Principle

1 The parties may, directly or by reference to rules of arbitration, determine the arbitral procedure; they may also submit the arbitral procedure to a procedural law of their choice.

2 If the parties have not determined the procedure, the arbitral tribunal shall determine it to the extent necessary, either directly or by reference to a statute or to rules of arbitration.

3 Regardless of the procedure chosen, the arbitral tribunal shall ensure equal treatment of the parties and the right of both parities to be heard in adversarial proceedings.

የጀርመን ህግ፦

Section 1042 General rules of procedure

(1) The parties shall be treated with equality and each party shall be given a full opportunity of presenting his case.

(2) Counsel may not be excluded from acting as authorised representatives.

(3) Otherwise, subject to the mandatory provisions of this Book, the parties are free to determine the procedure themselves or by reference to a set of arbitration rules.

(4) Failing an agreement by the parties, and in the absence of provisions in this Book, the arbitral tribunal shall conduct the arbitration in such manner as it considers appropriate. The arbitral tribunal is empowered to determine the admissibility of taking evidence, take evidence and assess freely such evidence.

## 7. የግልግል ዳኝነቱን ስለማሻር እና ስለማስፈፀም

ምንም እንኳ የግልግል ዳኝነት ከፍርድ ቤት ዉጭ ያለ የግጭት መፍቻ ስርዓት ነዉ ቢባልም ዞሮ ዞሮ ዉሳኔዉን ለማሰጠት ባለዉ ሒደት እንደነገሩ ሁኔታ ጣልቃ የሚገባባቸዉ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆኖ የግልግል ዉሳኔዉ ከተሰጠ በኋላም በህግ መሰረት በአግባቡ መወሰኑን በፍርድ ቤቶች ፍተሻ ሊደረግበት ይችላል። የግልግል ዉሳኔዉ ወደ ፍርድ ቤት የሚሔድበት አግባብ ተዋዋይ ወገኖች ዉሳኔዉን ለማሻር፣ ዉሳኔዉን በፍርድ ቤት እዉቅና ለማሰጠት ወይም ዉሳኔዉ በፍርድ ቤት እንዲፈፀምለት ለመጠየቅ ሊሆን ይችላል። የነዚህ ነገሮች አቀራረብ ግን እንደየ ሀገራት ህግ ይለያያል።

የግልግል ዉሳኔዉን በፍርድ ቤት ስለማፀደቅ፡- የግልግል ዉሳኔዉን በፍርድ ቤት ማፀደቅ በአንዳንድ ሀገሮች የግልግሉን ዉሳኔ በፍርድ ቤት ለማስፈጸም እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚቆጠር ነዉ። በዚህ ሂደት የመቀመጫዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔዉን ለማፅደቅ ዉሳኔዉ በተሰጠበት ሀገር/የመቀመጫዉ ህግ መሰረት የተሰወሰነ መሆኑን ያረጋግጣል። ለማፀደቅ የሚደረገዉ ማመልከቻ የሚቀርበዉ ዉሳኔዉ በተሰጠበት ሀገር ለሚገኝ ፍርድ ቤት ነዉ ማለት ነዉ። በአብዛኛዉ ሀገሮች ህግ ግን ዉሳኔዉን ለማፀደቅ የሚደረግ ማመልከቻ ሳያስፈልግም ዉሳኔዉን በፍርድ ቤት ማስፈፀም ይቻላል።

ሌላኛዉ አማራጭ በዉሳኔዉ ቅር የተሰኘ ወገን የተሰጠዉን የግልግል ዉሳኔ የፍርድ ባለመብት የሆነዉ ወገን እንዲፈፀምለት ፍርድ ቤት ከማመልከቱ በፊት የፍርድ ባለ ዕዳዉ ወይም ባለመብቱ ዉሳኔዉን ለማሻር ለፍርድ ቤት በማመልከት ፈራሽ ለማስደረግ ይችላል። ማመልከቻዉ የሚቀርበዉም ግልግሉ ተቀምጦበት በነበረበት ሀገር ፍርድ ቤት ነዉ።ዉሳኔዉን ፈራሽ ለማድረግ የሚቀርብ አቤቱታ በህግ የተቀመጡ መሰረቶችን ሲያሟላ ብቻ ነዉ። በጣም በብዙ ሀገሮች የግልግል ዳኝነቱን ፈራሽ ለማስደረግ አቤቱታ መቅረብ የሚችለዉ የግልግል ዳኝነቱን የፀና የማያደርጉ ምክንያቶች ሲኖሩ ነዉ።

በአብዛኛዉ ሀገሮች የግልግል ዳኝነት ዉሳኔዉን ለማሻር መሰረት የሚሆኑት የሚከተሉት ምክንያቶች ናቸዉ፡-

1. በግልግል ዳኝነቱ ሂደት ዳኞች የተመረጡበት አግባብ የህግ መሰረት የሌለዉ ሲሆን
2. የግልግል ዳኞች ዉሳኔዉን የሰጡት ገለልተኛነት በጎደለዉ ሁኔታ ሲሆን
3. የግልግል ዳኝነቱ ስነ ስርዓታዊ ፍትህ በጎደለዉ መልኩ ( አንደኛዉ ወገን የግልግል ዳኝነቱ የተጀመረ መሆኑን ሳያሳዉቅ ከቀረ፣ ተዋዋይ ወገኖችን እኩል የመሰመት እድል ሳይሰጣቸዉ የቀረ ከሆነ ............
4. የግልግል ዉሳኔዉ በግልግል ስምምነቱ ያልተካተቱ ጉዳዮች ላይ ዉሳኔ ካሳለፈ
5. የተሰጠዉ ዉሳኔ የመቀመጫዉን ሀገር ብሔራዊ ፖሊሲ የሚቃረን ሲሆን

በመጨረሻም የግልግል ዉሳኔዉን ዋጋ ሊያሳጣ የሚችለዉ በአፈፃፀም ወቅት የሚነሳ መቃወሚያ ነዉ። የፍርድ ባለመብት የሆነዉ ወገን የግልግል ዉሳኔዉን ለማስፈፀም ፍርዱን ሊፈፅምለት ወደሚችል ፍርድ ቤት በሚሄድበት ወቅት የፍርድ ባለዕዳዉ ዉሳኔዉ እንዳይፈፀም መቃወም ይችላል። የግልግል ዉሳኔዉን ለማስፈፀም የግልግሉ መቀመጫ ከሆነዉ ሀገር ዉጭ ባሉ ፍርድ ቤቶች ሊጠየቅ ይችላል። በተለይም አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነትን ለማስፈፀም ስምምነት በገቡ ሀገሮች ፍርድ ቤቶች ቢጠየቅ የበለጠ ዉጤታማ ይሆናል። የዉሳኔዉን መፈፀም ለመቃወም የሚያስችሉ ምክንያቶች ከሞላ ጎደል የግልግል ዉሳኔን ለማሻር ከሚቀርቡ ምክንያቶች ጋር ተመሳሳይነት አላቸዉ። በአጠቃላይ ተዋዋይ ወገኖችም ሆኑ የግልግሉ ዳኞች ዉሳኔዉን ለማሻር ወይም ከመፈፀም ለማቀብ የሚያበቁ ምክንያቶች ሳይከሰቱ  ተፈፃሚነት ያለዉ የግልግል ዉሳኔ ማሰጠት የሚቻልበትን ሁኔታ ሁሉ ቀድመዉ ማመቻቸት አለባቸዉ።